# ድህረ መለስ ኢትዮጵያ
## ቀጣይ ስርአት - ቀጣይ የጥፋት አዙሪት

በቅድሚያ ላለፉት 21 አመታት ኢትዮጵያን በገዙት አቶ መለስ ዜናዊ እረፍት ለቤተሰቦቻቸውና ለቅርብ ወዳጆ ቻቸው መፅናናትን እንመኛለን።

በአቶ መለስ ህልፈት ምክንያት "ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዴት?" የሚለው ጥያቄ እየተነሳ በተለይ ደግሞ ከእን ግዲህ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የፖለቲካ ምህዳሩን "ከፈት" ለማድረግ ይሞክራሉ ወይስ ከአፋኝና አሸባሪ ስርአታቸ ው በስተቀር ምንም አማራጭ የለንም ብለው ይገፉበታል? የሆነ ቢሆን ከዚህ አዲስ ሁኔታ አንፃር የሃገራችን ዴሞክራቶ ች ለቀጣዩ ትግል እንዴት ይዘጋጁ? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ በርካታ ውይይቶችና ክርክሮች እየተካሄዱ ነው። ለ ነዚህ ጥያቄዎች ትግል አጋዥ የሆነ መልስ ለመስጠት ከፈለግን ከሁሉ አስቀድሞ በመለስ ዜናዊ መሪነት የተተከለውን ከሱም እልፈት በኋላ የኢህአዴግ መሪዎች ከኛም አልፎ ለቀጣዩ ትውልድ ይፀናል የሚሉት ስርአት እጅግ አስከፊ የሆነ የጥፋት አዙሪት ገፅታ እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል። ምን አይነት የጥፋት አዙሪት?

ከሁሉ ከሁሉ በፊት የዚህ አገዛዝ ውድቀትና የችግራችን ሁሉ ምንጭ የሆነው በአመት ከአስር በመቶ በላይ " እድገት" ተመዘገበ እየተባለ ሌት ተቀን ከሚለፈፈው ፕሮፓጋንዳ በተፃራሪ ከሃገራችን ህዝብ አብዛኛው የሚገኝበት ዘግ ናኝና ከአመት አመት እየከፋና እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለው ማጣትና ድህነት ነው። ይህ የህዝባችን የሰቆቃ ኑሮ የሚለካ ው በተባበሩት መንግስታትም ሆነ በሌሎች አለም አቀፍ ተቋማት ከአመት አመት የሚወጡት በድህነትና በኑሮ ጉስቁል ና ዙሪያ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ኢትዮጵያን በአለም ከመጨረሻወቹ አምስት አገሮች አንዷ አድርገው በማስቀመጣቸው ብቻ አይደለም። ይባስ ተብሎ በእነዚሁ ጥናቶች በእድገትና በህዝብ ኑሮ መደላደል ስላለው ዝምድና ሲወሳ ከእድገት ጋር የሃብት ድልድልም ፍትሃዊ ሆኖ ድህነትም እየቀነሰ የሚሄደባቸው በርካታ አገሮች ሲኖሩ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ እድገት ልማትን እየተፃረረና ጥቂቶችን እያከበረ ብዙሃንን ደግሞ ለባሰ ድህነት እየዳረገ የሚሄድባቸው አገሮች ሲወሱ ኢትዮጵያችን ለዚህ አስከፊ ክስተት እንደምሳሌ ጣት የሚቀሰርባት አገር መሆኗ ነው። ይህ ጥቂቶች ሰማይ ጠቀስ ሃብ ት እያካበቱ ከሌሎች አገሮች ከበርቴዎች የማይተናነስ የተደንደላቀቀ ኑሮ የሚኖሩበት ብዙሃን ደግሞ ከአምናው ዘንድ ሮ እየከፋ ለሚሄድ ሰቆቃ የሚዳረጉበት ክስተት ሚልዮኖች በእለት ከእለት ኑሯቸው የሚያዩት ሃቅ ነው። ኢህአዴግ የ ዛሬ 21 አመት ዋና አላማየ ኢትዮጵያውያን በቀን ሶስቴ በልተው እንዲያድሩ ነው በሚል "ርሃብ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ" እያለ ሲሰነዝር ከቆየው "ዛቻ" አንፃር ሶስቴው ቀርቶ አንዴም አሮበት ህዝብ የበይ ተመልካች በሆነባት አገር በዚህ መ ልክ የባእዳንን ወይም የሃገር ምሁራንን ጥናቶች መጥቀሱ ለቀባሪ ማርዳት ስለሚሆንብን እዚህ ላይ ዝርዝር አንገባም።

የሃገራችን ችግሮች በሙሉ የሚመነጩትና በፖለቲካውም፣ በማህበራዊውም፣ በሰላሙም፣ በህዝቦች ወንድማ ማችነትም ሆነ በሃገር አንድነቱ መስክ የማንወጣው አስከፊ አዙሪት ውስጥ የጨመረን ይህ በኢህአዴግ የተተከለው ለ ጥቂቶች የተገነባና የህዝብ ደም መጣጭ የኢኮኖሚ ስርአት ነው። ህዝባችን ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ለመውጣት ዴሞክራ ሲያዊና ተጠያቂነት የነገሱበት ስርአት ያስፈልገዋል። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ደግሞ የዚህ ግፈኛ ስርአት ዘላቂነት እንዲረጋገጥ፣ በሚለፈፈውና በተጨባጭ ህዝባችን ከሚኖረው ጋር ያለው የከረፋና እየጎላ የሚሄድ ቅራኔ ሊያስነሳ የ ሚችለውን የአልሞት ባይ ተጋዳይ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለመግታት ከፈለጉ ብዙም አማራጮች የላቸውም። ልክ እንደ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ የኑሮ ሁኔታ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም ከእለት እለት ይባስ የሚረገጡበት፣ አነ ሱ ሲባሉ የሚቀነሱበት፣ ነገሮች ልክ አይደሉም በሚል የሚናገርና የሚፅፍ እንዳይኖር የፕሬስ ነፃነት ደብዛው የሚጠፋ በት፣ "በቃኝ" ለማለት የደፈረ ሁሉ በአሸባሪነት የሚፈረጅበት አፋኝና አሸባሪ አገዛዝ የመገንባቱን ጉዳይ የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገው ያቀርቡታል። የህዝብ ትግል አይሎ እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ከዚህ ሂደት እንዲያፈገፍጉ እስካልተደ ረገ ድረስ ማጣትና ድህነት እየከፉ ሲሄዱ ሽብርና አፈናም እየተባባሱ የሚሄዱበት አዙሪት ውስጥ ነን የምንለው ለዚህ ነው። እንግዲህ ከዚህ ስንነሳ ሁለት ጥያቄዎች ይኖራሉ። አንደኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ስትራቴጂያዊ አላማ ምን መሆን አለበት? ይህንን አላማ እውን ለማድረግ በሚደረገው ታሪካዊ ፍልሚያ ያለው የሃይሎ ች አሰላለፍ ምን ይመስላል?

እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች የምንመኘውና የምንታገልው ለስርአት ለውጥ እንደሆን ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ሃገራችንና ህዝባችን የሚያስፈልጓቸው ለውጥ ወይም ሽግግር እስካሁን በታሪካችን እንደታየው አንድ ድርጅት ወይም ሃይል ሌላውን ድርጅት ወይም ሃይል አሸንፎና ተክቶ የራሱን ስልጣን ለመጫን የሚሞክርበት የኪሳራ ሂደት አይደለም። የሚያስፈልገን ከዚህ እጅግ የሰፋና ህብረተሰባችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፀረ ዴሞክራሲ ወደ ዴሞክራሲያዊና የተጋጋ፣ አሸናፊና ተሸናፊ ሳይኖር ሁሉም በአሸናፊነት የሚወጣበት በብሄራዊ እርቅ ላይ የተገነባ የሽግግር ሂደት ነው። እንዲህ አይነቱ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት የመገንባት አላማ በሃገራችን ዴሞክራቶች ጎራ ሰፊ ተቀባይነት ያለው በጎ አካሄድ ነው። ይህንን ሰፊና አገራዊ አጀንዳ ካነገብንና ለዚህ እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ለሆነ ታሪካዊ ተጋድሎ ራሳችንን ብቁ ለማድረግ ከፈለግን ከሁሉ በፊት በዚህ ፍልሚያ ያለው የሃይል አሰላለፍ እንዴት ነው? ከዚያ ደግሞ ከዚህ አሰላለፍ አንፃር የመለስ ዜናዊ ህልፈት ምን የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከት ያስፈልጋል።

የወያኔ/ኢህአዴግን ሰፈር በተመለከተ እነሱ እንደሚሉትና አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ "በእንባ ጎርፍ እያጀበ አሳየ" እንደሚባለው ህዝባችን ከዳር ዳር የሚደግፉቸው አይደሉም። አንዳንድ ተቃዋሚዎች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ደግሞ ይህ ሃይል በህብረተሰቡ ውስጥ ማንንም የማይወክል፣ ከህብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ የተነጠለ ምንም መሰረት የሌለውና ገፍተር ቢያደርጉት ሊወድቅ የሚችል ሃይል አይደለም። ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ከአዲስ አበባ እስከ ዳር ድንበር መንደር ሌላው ቀርቶ በቤተሰብ ደረጃ ድረስ የወረደ የተዋቀረ ሃይል ነው። በአለፉት 21 አመታት በተለይ ደግሞ ከግንቦት 97 ወዲህ ባደረገው ደጋፊ የመሰብሰብና የማደራጀት ጥረት የተነሳ ዛሬ በተለይ ከወጣቱ የተወሰነ ሃይል መልምሎና አደራጅቶ ለስርአቱ ተናካሽ ወይም ቮካል የሆነ ጥቅሙን የሚያውቅ ትኩስ ሃይል አፍርቷል። እንደ መንግስት ሆኖ ደግሞ በሰራዊቱ፣ በመንግስት በጀት፣ በፖሊሱ፣ በመረጃ መረቡ፣ በመገናኛ ብዙሃን ላይ በብቸኝነት ባለው ቁጥጥር ይጠቀማል። ከዚህ አልፎም በተከለው የመሬት ስሪት አማካኝነት በደርዘን ሚልዮን ገበሬዎች ህልውና ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን አለው።

ከዚህ ድርጅታዊና መንግስታዊ አቅም  አንፃር የተቃዋሚውን ጎራ ብንመለከት ከኢህአዴግ የጥንካሬ ምንጮች አንዱም እንደሌለው እናያለን። በምን ምክንያት ይሁን በምን የኢህአዴግ ድርጅታዊ መዋቅርም፣ ጥንካሬም፣ አቅምም የለውም። ያለው የማይበገር ሃይል እነሱ ሊደርሱበት የማይችሉት ህዝባዊ ሃይል ብቻ ነበር። ነገር ግን ራሳችንን እናታልል ካላልን በስተቀር ዛሬ ህዝባችንን ከዳር ዳር አንቀሳቅሰን የትግሉ ማእከልና የበጎ ለውጥ አራማጅ ሃይል ለማድረግ የምንችልበት ሁኔታ ውስጥ አይደለንም። በተለይ በግንቦት 97 ማግስት በተደጋጋሚ በተፈፀሙ ስህተቶች፣ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ህዝባችንን የትግሉ መአከል ለማድረግ የምንከተላቸውና የጨበጥናቸው መፈክሮች ለህዝባችን ተጨባጭ የሰቆቃ ኑሮ አማራጮች ከማቅረብ ይልቅ "ራእይ ነክ" የሆኑ መፈክሮች ናቸው። በዚህም ምክንያት በህዝባችን አይን በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ንቀትን የተላበሰ የተአማኒነት ችግር አለብን።

በዚህ ጉዳይ ከሁለት አመት ተኩል በፊት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ኢዴሃህ) የተቃዋሚው ጎራ ያጣውን ተአማኒነት መልሶ እንዲያገኝ ከዚያም በኋላ ደግሞ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ትግል በወያኔ ኢህአዴግ የአፈናና የከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ ሳይበተን ቀጣይነት እንዲኖረው ምን ማድረግ ይጠበቅብናል በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፊ ትንተና አቅርበናል። ይህንን "**ለህዝባዊ የትግል ማእበል - ብቃት ያለው ህብረተሰብ፣ ብቃት አልባ አመራር**" በሚል ርእስ በመጋቢት 2003 አ.ም. ያወጣነውንና በተለያዩ ድረ ገፆች ለንባብ የበቃ ሰፊ ትንተና አንባቢ እንደገና እንዲመለከተው እንጋብዛለን።

በመለስ ዜናዊ ህልፈት ምክንያት በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከቀረቡት ትንተናዎችና ለስርአት ለውጥ ትግላችን ከተጠቆሙት አካሄዶች ሌላ የምንጨምረው ነገር አይኖርም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ከዚህ ተያይዞ የመለስ ህልፈት ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው አዙሪት አንፃር ምን የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ሰሞኑን ከሚያጎርፉት ልፈፋ ከተነሳን ከነሱ የሚሰጠው አጭርና ግልፅ መልስ ነው። "መለስ ኖረ አልኖረ ቀስ በቀስ የገነባነው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ ስርአት አለ። ይቀጥላል።" ባዮች ብቻ አይደሉም። ከዚህም ዘልቀ

ው ህዝባችን "በነቂስ ወጥቶ" ለመለስ አነባ የተባለውን ክስተት እያጎሉ በማውሳት የዚህ ግፈኛ ስርአት መቀጠል ከነሱ
አልፎ "የሰማኒያ ሚልዮን ህዝብ ራእይ" መሆኑን ሊያሳምኑን እየሞከሩ ናቸው።

በኛ በኩል ደግሞ ከእንግዲህ አገራችን በዚህ መንገድ ልትቀጥል አይገባም። አትችልምም። ለፖለቲካ እርቅ፣
ለህግ የበላይነትና ለዴሞክራሲ ለእውነተኛ ሰላምና ህዝብን ላካተተ ልማት አዲስ ጅማሮ አዲስ አጋጣሚ ተፈጥሯል።
እንጠቀምበት እንላለን። የፊውዳሉ ስርአት በየካቲት አብዮት በተደመሰሰ ማግስት፣ ወይም ኢህአዴግ የደርግን መንግ
ስት አሸንፎ ስልጣን በያዘ ማግስት ፣ ወይም ደግሞ የግንቦት 97 ምርጫ ሲጨናገፍ ለተረጋጋ ሽግግር ያመለጡት ታሪካ
ዊ አጋጣሚዎች ሁኔታ ዛሬም መደገም የለበትም። ለዚህ ደግሞ ይህ የድህነትና የሽብር አዙሪት ተሰብሮ በዴሞክራሲያ
ዊ ስርአት እንዲተካ፣ በተሳካ የብሄራዊ ሽግግር ሂደት በተረጋጋና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ህብረተሰባችን ፊቱን ወ
ደ ልማት እንዲያዞርና ከአስከፊ ድህነት እንዲላቀቅ ለማድረግ ለስርአት ለውጥ የሚደረገው ትግል መቀጠል ይኖርበታ
ል የሚል ጠንካራ እምነት አለን። ይህ ሃገራዊ አላማ ግቡን እንዲመታ ከፈለግን ደግሞ ህዝባችን ባለቤትነት ተሰምቶት
በነቂስ ወጥቶ በአንድ አቅጣጫ እንዲታገልና ለድል እንዲበቃ የመጀመሪያ መጀመሪያ "ተነስ ታገል" የሚለውን ጥሪያ
ችንን አምኖ እንዲንቀሳቀስ ቀስ በቀስ ተአማኒነትን የማጎልበት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። ይህ ራሱ አስቸጋሪ ሊሆን
ቢችልም ካለፈው ልምዳችን ትምህርት የቀሰመ አካሄድ ይኑረን ካልን ደግሞ ህዝባችን እንደገና ተንቀሳቅሶ እንደገና በ
ሽብርና በወያኔ/ኢህአዴግ አይቀሬ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ትጥቅ ፈትቶ የባሰ ጨለምተኝነት ውስጥ እንዳይወድቅ ከፍ
ተብሎ የተወሳው የኢዴሃህ ሰነድ በተጠቆመው መልክ የትግሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችለን እቅድ አውጥቶ የ
መንቀሳቀስ ግዴታ ይኖርብናል።

ይህ በዚህ እንዳለ ለሃያ አንድ ረዥም አመታት በህብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን በራሱ በድርጅቱ ውስጥ በአንድ ግ
ለሰብ ዙሪያ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለመገንባት በቅቶ የነበረው የኢህአዴግ አመራር ዛሬ ቁንጮውን ማጣቱ በቀጣዩ የት
ግል ሂደት ምንም ለውጥ አያመጣም፣ የመለስና ድህረ መለስ ኢትዮጵያም ሆነች ወያኔ/ኢህአዴግ እንዳሉ ይቀጥላሉ
ማለት አይደለም።

የመለስ ዜናዊ ስርአት የተገነባው በኢትዮጵያ ህዝብና በዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ላይ አፈናና ሽብር እያወረደ
ብቻ አይደለም። በወያኔ/ኢህአዴግ በራሱም ውስጥ ቢሆን በራእይና በአካሄድ ልዩነትም ሆነ በስልጣን ሽሚያ የሚነሱት
ን ግጭቶች የመለስ ዜናዊ አንጃ ሌሎቹን እየመታ፣ እያሰረ፣ እያባረረ ቀስ በቀስ በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ስር የወደቀ አ
ምባገነናዊ ስርአት ገንብቷል። የግለሰብ አምባገነኖች አነሳስና የስልጣናቸው ቀጣይነት የሚረጋገጠው አምባገነኑን ሊተካ
የሚችል፣ በሁሉም ዘንድ "እሱ ቢያልፍ እገሌ አለ" የሚባል ሌላ ግለሰብ ወይም ሃይል እንዳይኖር በዙሪያቸው የወራ
ሽ ወይም ተተኪ ሃይል ክፍተት ወይም "ቫኪዩም" በመፍጠር ብቻ እንደሆነ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሃቅ ነው። ድህረ
መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ከዚህ የምታመልጥበት ምንም ተአምር አይኖርም። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ለፕሮፓጋንዳ
ፍጆታ ሲባል ሽ ጊዜ መለስ ዜናዊ "በሰማንያ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ተተክቷል"፣ በአመራር ደረጃም ቢሆን "የመተ
ካካቱ" ሂደት በሰከነ ሁኔታ እየተከናወነ ነው ቢሉንም በሚቀጥሉት ወራት በአንድ ዘላቂ የሁነ "ሁነኛ" ተተኪ ላይ የ
መስማማት ችግር እንደሚኖርባቸው ግልፅ ነው። ቀጣዩ ውስጣዊ ግብግብ ሁለት ዋና ዋና ገፅታዎች ሊኖሩት ይችላሉ።

የመጀመሪያው የዴሞክራሲ ጥያቄ ይሆናል። በአንድ በኩል ሊነሱ ከሚችሉት የህዝባችን ዴሞክራሲያዊ ጥያ
ቄዎችና ሊከሰት ከሚችለው አለም አቀፍ ጫና አንፃር "ትንሽ ከፈት ካላልን የትም አንደርስም" የሚሉና በሌላ በኩል
ደግሞ መከፈት ማለት እንደ ግንቦት 97 በሩ ለጠላቶቻችን የሚበረገድበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል ብለው በለየለት
አፈናና ሽብር ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የማይታያቸው ወገኖች ይኖራሉ። በዚህ በዴሞክራሲ ጉዳይ የሚኖረው ሽኩ
ቻ ከጥቂት መሪዎችም ዘልቆ ሊሄድ የሚችልበትም ሁኔታ አለ። በድርጅቱ ውስጥ ባለው ሙሰኝነት የተመረረ፣ "ከበላ
ይ" ግንኙነት ባላቸው ካድሬዎች እየተረገጠ፣ እድገትና የኑሮ ሁኔታ በችሎታ ሳሁሆን በዘመድ አዝማድና በአምቻ ጋብ
ቻ በሙሰኝነት ሆኖበት አንገቱን የደፋ ካድሬም ቢሆን ይህ ሁኔታ ተቀይሮ የተሻለ ውስጣዊ ዴሞክራሲና ግልፅነት (ትራ
ንስፓራንሲ) ብሎ ሊነሳ ይችላል። ሁለተኛ ደግሞ የብሄሮች እኩልነትን የሚመለከት ይሆናል። ማንኛቸውም ቢሆኑ "እ
ንወክላለን" በሚሉት ብሄር ፊት አለን የሚሉት ተቀባይነት ምንም መሰረት የሌለው አባባል ነው። ሆኖም በጥቅም ግጭ
ቶች ሳቢያ በኢህአዴግ ውስጥ በተለይ ብሄርን አስመልክቶ ከአንዳንድ አይቀሬ ከሚሆኑ ማደናገሪያ "ማሻሻሎች" ዘል

ቆ በተጨባጭ የተመጣጠነ ውክልና በሚለው ጥያቄ ዙሪያ በአባል ድርጅቶች መሃከል ሌላ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች በመለስ ህልፈት ምክንያት ከተፈጠረው አዲስ ሁኔታ አንፃር የትግል ስትራቴጂያቸንን ስንቀይስ ከፍ ብለን ስለ ተአሚኒነት ግንባታ፣ የትግሉን ቀጣይነት ስለማረጋገጥ ግዴታ፣ ህብረተሰባችንን ወደ ዴሞክራሲያዊና በእርቀ ሰላም የተረጋጋ ሽግግር የሚለው ራእይና አጀንዳ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጭር ጊዜ ደግሞ ለዚህም አዲስ ክስተት የሚመጥን ታክቲክም እንደሚያስፈልገን ግልፅ ነው። በቀጣዩ ጊዜ ከዚህ አዲስ ሁኔታ ተነስተን ለትግላችን መግፋት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

1. ከዚህ ከመጭው ውስጣዊ ቅራኔና ትንንቅ አንፃር "ወያኔ/ኢህአዴግ ወያኔ/ኢህአዴግ ነው። ትግላችን ይህንን የጥፋት ሃይል በህዝብ ትግል አስገድዶ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ መገንባት ስለሆነ ይህ የውስጥ ግጭትና ትግል አይመለከተንም።" ከሚል አቋም መነሳት የለብንም። "ከፈት እንበል"፣ የአባል ድርጅቶች ብሎም የብሄሮች እኩልነት ይረጋገጥ ወዘተ እያሉ የሚንቀሳቀሱትን ሃይሎች ከአክራሪዎቹ እኩል አይናችሁን ለአፈር ማለት አይቻልም። ከዚህ ይልቅ በዚህ ለ21 አመት በተገነባው ፀረ ዴሞክራሲያዊና ዘረኛ ውቅያኖስ መሃል ወያኔ/ኢህአዴግ ብቻውን ተነጥሎ የዴሞክራሲና የእኩልነት ደሴት ሊሆን የሚችልበት ምንም ተአምር እንደማይኖር እንዲገነዘቡ መጣር ያስፈልጋል። በሃገር የሌለ ዴሞክራሲ በወያኔ/ኢህአዴግ ውስጥ ብቻ፣ ለሃገራችን ብሄሮች የተነፈገ እኩልነት ለዚህ ድርጅት አባሎች ብቻ ሊረጋገጥ የሚችልበት ምንም አይነት ተአምር አይኖርም። ከዚህም በመነሳት ትግሉ በዝግ ችሎት እስከተካሄደ ድረስ የትም እንደማያደርስ ተገንዝበው እነዚህ ሃይሎች ዴሞክራሲና የብሄሮች እኩልነት በመላ ህብረተሰቡ ይረጋገጥ በሚል አላማ በህዝብ ፊት በይፋ መሰለፍ እንዳለባቸው፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከጎናቸው እንደሚቆሙ በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

2. ለአባላትም ሆነ ለሰራዊቱና ፖሊሱ የአክራሪዎቹ መሰረታዊ ማስፈራሪያ ወይም ክርክር ከወዲሁ የምናውቀው ነው። ይኸውም " ተቃዋሚዎች የሚፈልጉት የስርአት ለውጥ ብሎ ነገር በዚህ ሳቢያ እኛ ደርግን ጥለን እንዳደረግነው ገዥውን ፓርቲ፣ ሰራዊቱን፣ ፖሊሱን ወዘተ በትነው፣ አባላቱን ለእስር፣ ለግድያ ለእርዛት በመዳረግ በህልውናቸው የሚመጣ መአት ይሆናል" በማለት እነዚህ ወገኖች ሌላው ቢቀር ለራሳቸው ሲሉ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት እንዲዋደቁ የሚሞክር አካሄድ ነው። ይህንን የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ፕሮፓጋንዳ ለማገዝ ካልፈለግን "ወያኔ/ኢህአዴግን እና ወድማለን" ከሚል ከአጉል ፕሮፓጋንዳ መቆጠብ ይኖርብናል። ከዚህ ይልቅ አንደኛ በህዝባዊ ሰላማዊ ትግል የስርአት ለውጥ ሲደረግ በሙሰኝነትና በግፈኝነታቸው በራሱ በሰራዊቱ ከተጠሉ ጥቂቶች በስተቀር መቼም ሆነ የትም ሰራዊትና ፖሊስ ፈርሶ በሌላ እንዳልተተካና ሁለተኛ ደግሞ የምንገነባው ስርአት ዴሞክራሲያዊ እንደ መሆኑ መጠን ድርጅታቸውም ራሱን አድሶና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ከመቀጠል የሚከለክለው ምንም ነገር እንደማይኖር አበክረው መናገር ይኖርባቸዋል። ከዚህም አልፎ "የመበተን" ነገር ከመጣ ያለው አደጋ ከዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በኩል የሚሰነዘር ሳይሆን "በታኞች" የሚሆኑት ዛሬ ከህዝቡና ከህብረተሰቡ የሚያናክሷቸውና ደም የሚያቃቧቸው አክራሪዎች ነገ ቀውጢ ሁኔታ ሲፈጠር ሃብታቸውንና ንብረታቸውን ወዳሸሹበት ባእድ አገር የሚፈረጥጡት ገዥዎች እንደሚሆኑ አስረግጦ መናገር ያስፈልጋል። ይህንን ሁሉ በመገንዘብ የወያኔ/ኢህአዴግ ግፈኛ ስርአት ሁሉንም ይዞ ገደል ከመግባቱ በፊት እነዚህ በድርጅቱ ውስጥ ዴሞክራሲና የብሄሮች እኩልነት የሚሉ ወገኖች ከመዘግየቱ በፊት ከህዝባዊው ትግል እንዲደባለቁ ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል።

3. እርግጥ ይህ የመጭው ትግላችን ዋና ገፅታ ሆኖ የሚታይ ነገር አይደለም። በኢህአዴግ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ትንንቅ እንደ ቀላል ነገር አንየው አልን እንጂ የሃገራችንን እጣ ፈንታ እሱ ላይ እናንጠልጥል ማለት አይደለም። ኢህአዴግ ተከፈተ አልተከፈተ የቆየ የአጭርና የረዥም ጊዜ አጀንዳችንን አንግበን ህዝባችንን ከእለት እለት ይበልጥ የትግሉ ባለቤት እያደረግን የምንቀጥልበት ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ፣

ሀ/ በአጭር ጊዜ አንፃር የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ፣ የፕሬስ ነፃነትን የሚያፍነው አዋጅ እንዲነሳ፣ በፀረ ሽብር ትግል ስም ማንኛውንም ህጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞ ለማፈን የሚጠቀሙበት ፀረ ሽብር አዋጅ እንዲሻር፣ የሲቪክ ማህበራትን ለማኮላሸት ተጠንስሶ በእርግጥም በሃገራችን በዚህ መስክ በቅድም ግንቦት 97 ወቅት በስንት መስዋእ

ትነት የተገነባው ሁሉ የፈራረሰበት ሁኔታ ውስጥ ስለሆንን እነዚህን ጥያቄዎች አንግቦ በውስጥም በአለም አቀፍ ደረጃ ም በሰፊውና በአንድነት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ለ/ ወደምንፈልጋት አዲስ ኢትዮጵያ የሚደረገው የትግል ጉዞ ወሳኝ ምእራፍ የሚደርሰው ለዴሞክራሲ የሚ ደረገው ህዝባዊ ትግል አይሎ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ ሲሰየም እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። ይህ አገር አቀፍ የሽግግር ጉባኤም በህዝብ ትግል በውስጡ ዴሞክራሲያዊ ተሃድሶ ማካሄድ መገደድ የሚኖርበትን ወያኔ/ ኢህአዴግንም ጨምሮ በሃገርም ሆነ በውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ማህበራትና ስብስቦች፤ የሙ ያ ማህበራት፤ የምሁራን የወጣቶች የሴቶችና ሌሎች ማህበራት ተወካዮች እንዲሁም ከሃገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የ ሚጋበዙ የሃገር ሽማግሎችና የሃይማኖት አባቶች የሚገኙበት እጅግ ሰፊ ጉባኤ ይሆናል።

ሐ/ ከፍ ብለን እንደጠቆምነው እነዚህን የአጭርና የረዥም ጊዜ አጀንዳዎች እውን ለማድረግ በህዝባዊ ትግል የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ከጥፋት ሂደታቸው እንዲገቱ ማድረግ የማይታለፍ ግዴታ ነው። ለዚህ ደግሞ ቀደም ብለ ን በጠቀስነው የኢዴሃህ ሰነድ በቀረበው መልክ

* ዛሬ በህብረተሰባችን አስከፊ የሆነ ጨለምተኝነት ነግሷል፣ ትጥቅ መፍታት አለ፣ ተቃዋሚው ጎራ በህዝባች ን ፊት ጨርሶ ተአማኒነት አጥቷል ከሚለው ሃቅ ተነስቶ ይህንን ለመወጣት ምን አጀንዳ ይዘን እንንቀሳቀስ? ይህ ትግል ከተሳካልን ደግሞ እንደ ገና በሽብርና በኢህአዴግ መሪዎች የከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ መልሶ እንዳይፈታ ምን እናድርግ ?

* በሃገር ውስጥም ቢሆን ቀጣይነት የሚኖረው ህዝባዊ የትግል እምርታ ለመፍጠር በህጋዊነት የሚንቀሳቀሱ የ ፖለቲካም ሆነ የሲቪል ሶሳይቲው ድርጅቶች በአሉበት እጅግ ፈታኝ ሁኔታም ውስጥ ሆነው ለትግሉ ከአሁኑ ይበልጥ የ ሚያመረቃ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በሚያነግቧቸው መፈክሮችም ሆነ በአደረጃጀታቸው ይበልጥ ብቁ ሆነው እንዲን ቀሳቀሱ እንዴትና ምን ማድረግ ይቻላል? ትግላቸውንስ በምን ዘዴ ልንረደር እንችላለን?

* በሃገር ቤት ህዝባዊ ትግሉን ለመቀስቀስም ሆነ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ሁሉም ብሶቱን አንግቦ እንዲንቀሳቀስ፣ ሁሉም ብሶትህ ብሶቴ ብሎ እንዲተጋገዝ፣ ሁሉም ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት ያለው አንድ አማራጭ የስ ርአት ለውጥ መሆኑን አምኖ ለዴሞክራሲ እውንነት በአንድ አቅጣጫ እንዲገፋ ብለን በሰነዱ ለጠቀስነው "ሶስትዮሽ" ስትራቴጂ እውንነት በወጣቱ፣ በሰራተኛው፣ በገበሬው፣ በነጋዴው፣ በኢንቬስተሩ፣ በሴቶች፣ በመንግ-ስት ሰራተኞች፣ በስራ አጦች፣ በጎዳና ተዳዳሪዎች ወዘተ ዙሪያ አንቀሳቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ግንባር ቀደም ሃይሎች አስተማማኝ የሆነ የ ህቡእ ታግሎ አታጋይ መዋቅር እንዲዘረጉ በምን ዘዴ ልንረዳ እንችላለን?

እነዚህ ሁሉ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ጥያቄዎች የግል ድርጅትን ሳይሆን ህዝብንና ሃገርን በሚያስቀድም መልክ በሚካሄዱ ውይይቶች መቋጠር ይኖርባቸዋል። ከዚህ ውይይት የጋራ ትግል ማኒፌስቶ ማፅደቅና ይህንን ተግባራዊ ለ ማድረግ ደግሞ አሁን ባሉት ስብስቦች ትብብር የጋራ ታግሎ አታጋይ አካል የመፍጠሩ ጉዳይ ትኩረት የምንሰጠው ሃገ ራዊ አደራ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ዛሬ ለህዝብና ለኢትዮጵያ እንቆማለን የሚሉ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድ ርጅቶች አንገብጋቢና አጣዳፊ ተግባር እንዲህ አይነቱን ውይይት እያበራቱ ወደ አንድ የጋራ መፍትሄ የምንሄድበትን ጎ ዳና ማዘጋጀት ይመስለናል። በዚህ በኩል ድርጅታችን በአባልነት በሚሳተፍበት "የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ም" ሆነ ከሌሎች ስብስቦችም ጋር በመተባበር የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን እናረጋግጣለን።

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
መስከረም 2005